# በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሚደረገው ተቃውሞ ዛሬም ቀጥሎ ዋለ

December 13, 2017




በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች እየተደረገ ያለው ጸረ ሕወሓት ተቃውሞ ዛሬም ቀጥሎ ዋለ” ከየአካባቢዎቹ የወጡት መረጃዎች እንዳመለከቱት፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ደብረታቦር፣ ወልድያ፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች ኃይለኛ ተቃውሞ እየተካሔደ ይገኛል” በየዩኒቨርሲቲዎቹ የተሰማሩት የህወሓት ስልጣን ጠባቂ አጋዚ ወታደሮች በተማሪዎች ላይ ማንኛውንም ጥቃት እየወሰዱ ሲሆን፣ በጥቃቱም የሞቱ፣ የቆሰሉ እና የተጎዱ ተማሪዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል” ከሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች አንድ ቀን ዘግይቶ ተቃውሞ የጀመረው ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲም ተማሪዎች ተቃውሞ እያሰሙ እንደሚገኙ ታውቋል” በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ የተፈጸመውን ጥቃት በመቃወም የመጀመሪያውን የተቃውሞ ድምጽ ያሰማው ወልድያ ዩኒቨርሲቲ፣ ዛሬም ቀጥሎ በዋለው የተማሪዎች ተቃውሞ የተነሳ መደበኛው ትምህርት መቋረጡ ተሰምቷል”

በተመሳሳይ ሁኔታ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ቀጥሎ ሲውል፣ ተማሪዎችም በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳልተገኙ መረጃዎች ጠቁመዋል” የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ከክልሉ የተወሰኑ ባለስልጣናት ጋር በመሆን፣ ተማሪዎቹን ለማነጋገር ያደረጉት ጥረት እንዳልተሳካም ተነግሯል” በርከት ያሉ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችም ግቢውን ለቅቀው መውጣታቸውን ለመረዳት ተችሏል”  አምቦ እና ወለጋ ዩኒቨርሲቲም ቢሆን መረጋጋት እንደሌለ የጠቆሙት እማኞች፣ በዚህም የተነሳ የትምህርት

አሰጣጡ ታውኳል ብለዋል- እማኞቹ” በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለተቀሰቀሰው ተቃውሞ ዋነኛ መነሻ ምክንያቱ፣ የአዲግራት ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የሆኑ የትግራይ ተወላጆች፣ የአማራ እና ኦሮሞ ተወላጅ በሆኑ ተማሪዎች ላይ የፈጸሙት ጥቃት መሆኑ ይታወቃል” በተያያዘ ዜና፤ በትግራይ ክልል በሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎች ማለትም አዲግራት፣ አክሱም እና መቀሌ መረጋጋት አለመኖሩ ታውቋል” ለዚህ ሁሉ ተቃውሞ መነሻ የሆነው አዲግራት ዩኒቨርሲቲ፣ ትምህርት የተቋረጠ ሲሆን፣ የዩኒቨርሲቲው ተማሪ በሆኑ የሌላ ብሔር ተወላጆች ላይ አሁንም ጥቃት እንደሚሰነዘር ተሰምቷል” ጥቃቱ አልፎ አልፎም ቢሆን፣ አሁንም ሙሉ በሙሉ እንዳልቆመ የጠቆሙት መረጃዎች፣ ጥቃቱ ያነጣጠረውም በአማራ ተወላጆች ላይ መሆኑን መረጃዎቹ አክለው ገልጸዋል” እንዲሁም በአክሱም ዩኒቨርሲቲ ተመሳሳይ እርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ እነዚሁ የመረጃ ምንጮች ያረጋግጣሉ”